# ንጋት ኢንሹራንስ ብሮከር አክሲዮን ማኅበር የተሻሻለው መመስረቻ ጽሑፍ

## መግቢያ

እኛ ከዚህ በታች ስማችን፣ ዜግነታችንና፣ አድራሻችን ከዚህ በታች የተገለፀው መስራቾች በኢትዮጵያ ሕግ፣ በተለይም በ1952 ዓ.ም. በወጣው የንግድ ሕግ መሰረት የአክሲዮን ማኅበር ለማቋቋም በመወሰን ይህን መመስረቻ ጽሑፍ እና ከዚህ ጋር የተያዘውን የመተዳደሪያ ደንብ አውጥተን የማኅበሩን ካፒታል በስማችን አንፃር የተመለከተውን አክሲዮን በመግዛት በኢፌደሪ ፍትህ ሚኒስቴር የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ በአዲስ አበባ(ዋናው መስሪያ ቤት) በቁጥር ዋ/መ/5199/4U/2003 በቀን 22/9/2003 በመፈረም ለአለፉት 11 ዓመታት ስንንቀሳቀስ ቆይተናል፡፡

ሆኖም የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የንግድ ሕግ 2013 ዓ.ም አንቀፅ 255 የአክስዮን ማኅበራት የሚቋቋሙት በመመስረቻ ጽሑፍ እንደሚሆን በተደነገገው መሰረት ቀደም ሲል የተዘጋጀውን መተዳደሪያ ደንብና መመስረቻ ጽሑፍ አንድ ወጥ በሆነው በዚህ መመስረቻ ጽሑፍ አጠቃልለን አቅርበናል፡፡

### አንቀፅ አንድ

### የማኅበሩ መጠሪያ

የማኅበሩ መጠሪያ ስም ንጋት ኢንሹራንስ ብሮከር አክሲዮን ማኅበር ነው፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ NATIONAL BANK OF ETHIOPIA 52

### አንቀፅ ሁለት

### የማኅበሩ ዋና መ/ቤት

የማኅበሩ ዋና መስሪያ ቤት አዲስ አበባ ከተማ፣ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ፣ ቀበሌ 10፣ የቤት ቁጥር 180 ነው፡፡

### አንቀፅ ሦስት

### የባለአክሲዮኖች ስም፣ ዜግነትና አድራሻ

| ተ.ቁ | የባለ አክስዮኑ ስም | ዜግነት | አድራሻ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ክልል/ከተማ | ክፍለ ከተማ/ወረዳ | ቀበሌ | የቤት ቁጥር |
| 1. | ኮ/ል ትዕግስቱ ሣህሌ ገቤ | ኢትዮጵያዊ | አዲስ አበባ | ቦሌ | 02 | 182 |
| 2. | ወ/ት አድያም ትዕግስቱ ሳህሌ | ኢትዮጵያዊት | አዲስ አበባ | ቦሌ | 02 | 182 |
| 3. | ወ/ሮ ልድያ ትዕግስቱ ሳህሌ | ኢትዮጵያዊት | አዲስ አበባ | ቦሌ | 02 | 182 |
| 4. | አቶ መሳይ ትዕግስቱ ሳህሌ | ኢትዮጲያዊ | አዲስ አበባ | ቦሌ | 02 | 182 |
| 5. | ዶ/ር ፌቨን ትዕግስቱ ሳህሌ | ኢትዮጲያዊት | አዲስ አበባ | ቦሌ | 02 | 182 |
| 6. | አቶ ኃይለሚካኤል ከምባታ አላካ | ኢትዮጵያዊ | ኦሮሚያ | አድአ | 02 | 1083 |
| 7. | ወ/ሮ አሰለፈች ኃይለስላሴ ተሰማ | ኢትዮጵያዊት | ኦሮሚያ | አድአ | 02 | 1083 |
| 8. | ወ/ሮ ሲሳይ ኃይለሚካኤል ከምባታ | ኢትዮጵያዊት | አዲስ አበባ | አራዳ | 05 | 269/2 |
| 9. | አቶ አቤል ኃይለሚካኤል ከምባታ | ኢትዮጵያዊ | ኦሮሚያ | አድአ | 02 | 1083 |

## አንቀፅ አራት

## የማኅበሩ ዓላማዎች

ማኅበሩ የተቋቋመበት ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው።

1.የነባርም ሆነ የታሳቢ ደንበኞች የኢንሹራንስ ፍላጎት መለየትና ማማከር፣ የኢንሹራንስ መግቢያ ዋጋ መሰብሰብ፣ መተንተን፣ ውል ማዋዋል፣ የውል ዕድሳትና የካሳ ጥያቄዎች መከታተል፣ እና

2.ከማህበሩ ዓላማ ጋር ተዛማጅ የሆኑን ሌሎች ስራዎችን መስራት።

## አንቀጽ አምስት

## የማኅበሩ ዋና ገንዘብ

1.የማኅበሩ የተፈረመ ካፒታል ብር 3,222,000.00 (ሶስት ሚሊየን ሁለት መቶ ሃያ ሁለት ሺሀ) ነው።

2.የማኅበሩ የተፈረመ ካፒታል እያንዳንዳቸው ብር 1,000.00 (አንድ ሺሀ ) ዋጋ ባላቸው በጠቅላላው 3,222 (በፊደል ሦስት ሺሀ ሁለት መቶ ሃያ ሁለት) ተራ አክሲዮኖች ተደልድሏል።

3.የማኅበርተኞች የአክሲዮን ድርሻ በሙሉ ተከፍሏል።

4.የማኅበርተኞች የአክሲዮን ድርሻ የመዋጮ መጠን እንደሚከተለው ተገልጿል።

| ተ.ቁ | የባለ አክስዮኑ ስም | የአክሲዮን ድርሻ (%) | የአክሲዮን ድርሻ (%) መጠን | የተከፈለ የመዋጮ መጠን በብር |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ኮ/ል ትዕግስቱ ሣህሌ ጊቤ | 51.99 | 1675 | 1,675,000.00 |
| 2. | ወ/ት አድያም ትዕግስቱ ሳህሌ | 4.53 | 146 | 146,000.00 |
| 3. | ወ/ት ሊዲያ ትዕግስቱ ሳህሌ | 2.51 | 81 | 81,000.00 |
| 4. | አቶ መሰይ ትዕግስቱ ሳህሌ | 0.78 | 25 | 25,000.00 |
| 5. | ዶ/ር ፊቨን ትዕግስቱ ሳህሌ | 0.19 | 6 | 6,000.00 |
| 6. | አቶ ኃይለሚካኤል ከምባታ አላካ | 34.33 | 1106 | 1,106,000.00 |
| 7. | ወ/ሮ አሰለፈች ኀ/ስላሴ ተሰማ | 1.67 | 54 | 54,000.00 |
| 8. | ወ/ሮ ሲሳይ ኃይለሚካኤል ከምባታ | 3.16 | 102 | 102,000.00 |
| 9 | አቶ አቤል ኃይለሚካኤል ከምባታ | 0.84 | 27 | 27,000.00 |
| | **ድምር** | **100** | **3,222** | **3,222,000.00** |

## አንቀፅ ስድስት

## አክስዮኖች

የማኅበሩ አክሲዮኖች ከአንድ እስከ ሶስት ሺሀ ሁለት መቶ ሃያ ሁለት ቁጥሮች ተሰጥቷቸዋል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ NATIONAL BANK OF ETHIOPIA 52

## አንቀፅ ሰባት

## የትርፍ አከፋፈል ሁኔታ

1.በየሂሳብ ዓመቱ መጨረሻ የማኅበሩን ንብረት እና ዕዳ የሚያሳይ የሂሳብ ሚዛን/ ባላንስ ሺት/ ተዘጋጅቶ ለዲሬክተሮች ቦርድ ይቀርባል፡፡

2.የማኅበሩ ዓመታዊ የሂሳብ ሁኔታ የሚያሳዩ ሰነዶች፣ ማለትም የሂሳብ ሚዛን /ባላንስ ሺት/፣ የትርፍና ኪሳራ መግለጫ፣ የንብረት ቆጠራ፣ የዲሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት እና የኦዲተሮች ሪፖርት በማኅበሩ መዝገብ ላይ ለተመዘገቡ ባላአክሲዮኖች ቢያንስ ከመደበኛው ጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ ቀን 24 ቀን አስቀድሞ በማኅበሩ ውስጥ ተመዝግቦ በሚገኘው አድራሻቸው ይላካል፡፡

3.በዓመቱ ሂሳብ መግለጫ ውስጥ የሚታየው የማኅበሩ የዓመቱ ገቢ፣ ጠቅላላ ወጪና፣ አላቂ ለሚሆኑ ነገሮች መተኪያ ገንዘብ /አሞርታይዜሽን/ አላዋንስ እና ለሌሎች መዋጮዎች ታክስና ያለፈው ዓመት ግዴታዎች ከተቀነሱ በኋላ የሚታየው የተጣራ ትርፍ ነው፡፡

4.ከተጣራው ዓመታዊ ትርፍ ላይ፡-

ሀ. የጠቅላላ የካፒታሉን 5% እስከሚያክል ድረስ በየዓመቱ 5% ለሕጋዊ መጠባበቂያ ይያያዛል፡፡

ለ. በጠቅላላ ጉባዔው ውሳኔ የፀደቁ ሌሎች ልዩ የመጠባበቂያ ሂሳቦችና የአሞርታይዜሽን ወጪዎች ከተቀነሱ በኋላ ተራፊው በተከፈለው የአክሲዮን ድርሻ ልክ ለባለአክስዮኖች ይከፋፈላል፡፡

5.የትርፍ ክፍፍል ድርሻዎች ለባለአክሲዮኖች የሚከፋፈልበት ጊዜና ሁኔታ በጠቅላላ ጉባዔ ይወሰናል፡፡

## አንቀፅ ስምንት

## የማኅበሩ የአስተዳደር ክፍሎች

የማኅበሩ የአስተዳደር ክፍሎች፡-

1.የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ፣

2.የዲሬክተሮች ቦርድ፣

3.ሥራ አመራር ፣

4.የውጭ ኦዲተር እና

5.ፀሀፊ ናቸው

## አንቀፅ ዘጠኝ

## ጠቅላላ ጉባዔ

የባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ከፍተኛ የሥልጣን አካል ነው፡፡ ይህም ጉባዔ መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎች ይኖሩታል፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ NATIONAL BANK OF ETHIOPIA 52

## አንቀፅ አስር

## የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ስልጣንና ተግባራት

1.የዚህ ሕግ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔው የሚከተሉት ስልጣንና እና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

ሀ.የዳሬክተሮች ቦርድ አባላትን ከመካከሉ ይመርጣል፣ ይሾማል፣ ይሽራል፡፡

ለ.የውጭ ኦዲተሮችን ይሾማል፣ ይሽራል፣ አበላቸውንም ይወስናል፡፡

ሐ.ሌሎች በሀግና ማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ መሰረት ለጠቅላላ ጉባዔ የተፈቀዱ ተግባሮች ይኖሩታል፡፡

## አንቀፅ አስራ አንድ

## የባለአክሲዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ስልጣንና ተግባራት

አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

1.የማኅበሩን መመስረቻ ፅሁፍ የማሻሻል፣

2.የማኅበሩን ዋና ገንዘብ የማሳደግ ወይም የመቀነስ፣

3.የማኅበሩን ዜግነት የመለወጥ፣

4.ማኅበሩ እንዲፈርስ ወይም ወደ ሌላ ዓይነት የንግድ ማኅበር እንዲለወጥ፣ እንዲከፋፈል ወይም እንዲዋሀድ የመወሰን፣

5.ሌሎች በሕግ ወይም በመመስረቻ ጽሑፍ በዚህ ጉባዔ እንዲታዩ ተለይተው የተሰጡትን ጉዳዮች የመወሰን፣ እና

6.በዚህ አንቀፅ ላይ የተመለከተው ቢኖርም የማኅበሩን ባለአክሲዮኖች ስም፣ አድራሻ፣ ዜግነት፣ የያዙት የአክሲዮን ብዛትና የተከፈለውን የገንዘብ መጠን በተመለከተ የሚደረጉ ለውጦች የማኅበሩን መመስረቻ ጽሑፍ እንደማሻሻል አይቆጠርም፡፡

## አንቀፅ አስራ ሁለት

## አጀንዳ

1.የጠቅላላ ጉባዔ የአጀንዳ ግልባጭ ከመጥሪያው ጋር ተያይዞ ለባለአክሲዮኖች ይላካል፡፡

2.ጉባዔው በሚካሄድበት ጊዜ የጠቅላላ ጉባዔው አጀንዳ ሊሻሻል ይችላል፡፡ ይህ ሊሆን የሚችለው ግን እንዲመርጡ የተፈቀደላቸው ይበልጡን /አብዛኛው/ የአክሲዮን ድርሻ የያዙት ሲስማሙበት ብቻ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
NATIONAL BANK OF ETHIOPIA
52

## አንቀፅ አስራ ሶስት

## የዲሬክተሮች ቦርድ ሥልጣንና ተግባራት

1.የዲሬክተሮች ቦርድ በሕግ፣ በማህበሩ የመመስረቻ ጽሑፍ ወይም በጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔዎች የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት የመፈፀም ግዴታ አለበት፣ ይህ ጠቅላላ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩበታል።

ሀ.የማኅበሩን ፋይናንስ የማስተዳደር፤ ማኅበሩ በቂ ዋና ገንዘብ እና ክፍያዎችን በወቅቱ የመፈፀም አቅም ያለው መሆኑን የማረጋገጥ፤

ለ.የማኅበሩ አስተዳደራዊ አደረጃጀት የማኅበሩን የፋይናንስ መግለጫዎችን እና ቁመናን ለመቆጣጠር የሚያስችል መሆኑን የማረጋገጥ፤

ሐ.የማኅበሩን ለአደጋ ተጋላጭነት እና ውስጣዊ አሰራር ለመቆጣጠር የሚያስችል በቂ የአሰራር ስርዓት የመዘርጋት፤

መ.የሚንቀሳቀሱና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች የመግዛት፣ የመሸጥና የማስወገድ፣ እና

ሠ.በማኅበሩ ላይ ጉዳት እንዳይደርስ የመከላከል፤ መከላከል ካልተቻለም ሊደርስ የሚችለውን አሉታዊ ተፅዕኖ የመቀነስ፤

2.ከላይ በአንቀፅ 1 ከንዑስ አንቀፅ (ሀ) እስከ (ሠ) የተዘረዘሩት እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የሚከተሉት ኃላፊነቶች አሉበት።

ሀ.የማህበሩ ባለአክሲዮኖች እና የቦርድ ስብሰባዎች ቃለ ጉባዔ፣ የሒሳብ መዝገብ፣ የባለአክሲዮኖች እና የዳይሬክተሮች መዛግብት እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶች እንዲያዙ የማድረግ፤

ለ.የሒሳብ መዛግብት ለኦዲተሮች ቦርድ በአስፈላጊው ጊዜ ሁሉ እንዲቀርብ የማድረግ፤

ሐ.የፋይናንስ እንቅስቃሴን ያካተተ ዓመታዊ የስራ አፈፃፀም ሪፖርት ለጠቅላላ ጉባዔ የማቅረብ፤

መ.በዚህ ሕግ ወይም በመመስረቻ ጽሑፍ መሰረት የማኅበሩን ጉባዔዎች የመጥራት፤

ሠ. የማህበሩ ዋና ገንዘቡ ¾ (ሶስት አራተኛ) በኪሳራ ባጣ ጊዜ ወዲያውኑ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ የመጥራት፤

ረ.በዚህ ሕግ፣ በመመስረቻ ጽሑፍ ወይም በማኅበርተኞች ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ መሰረት የመጠባበቂያ ገንዘብ የማቋቋም እና የመያዝ፤ እና

ሰ.የማኅበሩ ዕዳውን የመክፈል አቅም እየቀነሰ ከሄደ ወይም ዕዳውን መክፈል ካቋረጠ እንደነገሩ ሁኔታ ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ስነ ስርዓት፣ ዕዳን መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት ወይም የመክሰር ሥነ ሥርዓት እንዲጀመር ወይም እንዲከፈት የማድረግ።

ሸ.ከፀሐፊዎችና /ከለርክስ/ ከሌሎች ሰራተኞ በቀር የሥራ ኃላፊዎችን መሾም፣ የመመወዛቸውን መተመን ስጦታን ስንብትን ጡረታን በሚመለከት የመወሰን፣ እና

ቀ.ማናቸውንም ተስማሚ ሆኖ ያገኘውን የማኅበሩን ገንዘብ ስራ ላይ ስለማዋል ሃሳብ ለጠቅላላ ጉባዔው ሐሳብ የማቅረብ

3.የዲሬክተሮች ቦርድ አስፈላጊ እስከሆነ ድረስ ስልጣኑን ለሰብሳቢው ለመስጠት ይችላል፡፡

4.ቦርዱ በክፉ ልቦና፣ በተንኮል ወይም ከተሰጠው ስልጣን ውጭ ካልሰራ በቀር የተጣለበትን ኀላፊነት በመወጣት ወይም በዚህ የመመስረቻ ጽሁፍ መሰረት ኀላፊነት አይኖርበትም፡፡

5.የማኅበሩ ዲሬክተሮች በንግድ ሕግ አንቀጽ 307 የተመለከቱትን ቅድመ ሁኔታዎች ከአሟሉ ከሦስተኛ ወገን ጋር ላሉባቸው ግዴታዎች ዋስ መሆን ወይም ንብረቱን በዋስትና ማስያዝ፣ ከማኅበሩ ገንዘብ ሊበደሩ ወይም ለግል ዕዳቸው በማኅበሩ ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡

## አንቀፅ አስራ አራት

## የዲሬክቶች ቦርድ አባላት

1.ማኅበሩ የሚተዳደረው በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ በሚመረጡ በስድስት የዲሬክተሮች ቦርድ አባላት ይሆናል፡፡

2.በዚሁ መሰረት የሚቀጥሉት የአክሲዮን ማኅበሩ አባላት  የዲሬክተሮች ቦርድ አባላት ሆነው ተመርጠዋል፡፡

- ወ/ት አድያም ትዕግስቱ ሣህሌ፣
- ኮ/ል ትዕግስቱ ሣህሌ ጊቤ፣
- አቶ ኃይለሚካኤል ከምባታ አላካ፣
- ወ/ሮ ሊዲያ ትዕግስቱ ሣህሌ፣
- ወ/ሮ ሲሳይ ኃይለሚካኤል ከምባታ፣ እና
- አቶ መሳይ ትዕግስቱ ሣህሌ

3. የቦርዱ የስራ ዘመን ሶስት ዓመት ይሆናል፡፡

4.የዲሬክተሮች ቦርድ ከአባሎቹ አንዱን ሰብሳቢ አድርጎ ይመርጣል፡፡

5.ወ/ት አዲያም ትዕግስቱ ሣህሌ የዲሬክተሮች ቦርድ ሰባሳቢ ሆነው ተመርጠዋል፡፡ እና

6.የዲሬክተሮች ቦርድ አባል የተመረጠበት ጊዜ ካበቃ እንደገና ሊመረጥ ይችላል፡፡

## አንቀፅ አስራ አምስት

## ስለ ሥራ አመራር

1.የማኅበሩ የአስተዳደር ሥራ የሚመራው በዲሬክተሮች ቦርድ ተመርጦ የሚሾም የአገልግሎት ክፍያው እና አገልግሎት የሚሰጥበት ሁኔታ በሚወሰንለት ዋና ስራ አስኪያጅ ይሆናል፡፡

2.ሥራ አስኪያጁ የማህበሩን ጠቅላላ የዕለት ተዕለት ሥራዎች ይመራል፡፡ የዚህ አንቀፅ አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ስራ አስኪያጁ የሚከተሉት ተግባራት ይኖሩታል፡፡

ሀ.የማኅበሩን ዓመታዊ በጀት፣ የስራ ፕሮግራም እና የሂሳብ ሪፖርት እንዲሁም ሌሎች እንቅስቃሴዎችን ካዘጋጀና ከመረመረ በኋላ ለቦርዱ ማቅረብ።

ለ.ሠራተኛ መቅጠር፣ ዕድገት መስጠት፣ መስጠት፣ ማስተዳደር የደመወዝ ክፍያና ስራ ሁኔታዎች መወሰን፣ ለዋናው ስራ አስኪያጅ በቀጥታ ተጠሪ የሆኑትን ኃላፊዎች መርጦ እንዲሾሙ ለቦርዱ የማቅረብ።

ሐ.የማኅበሩን ዓመታዊ ሂሳብ የሚመረምሩ የውጭ ኦዲተሮችን ምርጫና ሹመት በሚመለከት ለቦርድ ሃሳብ /ምክር/ የማቅረብ።

መ. የቁጥጥር መዋቅር የመዘርጋት።

ሠ. በሰራተኞች ላይ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን የመውሰድ።

ረ.ቦርዱ በሚወስነው መሰረት በማኅበሩ ስም የባንክ ሂሳብ የመክፈት፣ የማንቀሳቀስ፣ ቼኮችንና ሌሎች ንግድ ሰነዶችን የማረጋገጥ፣ በማኅበሩ ስም ብድሮችንና ውሎችን የመፈራረም።

ሰ.በማኅበሩ ስም ራሱ ወይም ጠበቃን ወክሎ የመክሰስና የመከላከል፣

ሸ.ለማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ ተቃራኒ ካልሆነ በስተቀር ከሶስተኛ ወገኖች ጋር ግንኙነት በማድረግ ማኅበሩን የመወከል፣ እና

ቀ.ከላይ ከተጠቀሱት ተግባሮች ጋር የተዛመዱ ሌሎች ስራዎችንም የማከናወን።

3.አቶ ኃይለሚካኤል ከምባታ አላካ የአክስዮን ማኅበሩ ዋና ስራ አስኪያጅ ሆነው ተሹመዋል።

## አንቀፅ አሥራ ስድስት

## የማኅበሩ የስራ ሪፖርት

1.እያንዳንዱ ሂሳብ ዓመት በሚዘጋበት ጊዜ የዲሬክተሮች ቦርድ በማኅበሩ ያሉትን ልዩ ልዩ ንብረቶችና ዕዳዎች የሚያመለክትና የንብረቱን ዝርዝር የሚይዝ መዝገብ ያደራጃል።

2.ዲሬክተሮች ቦርድ የዓመቱን የሂሳብ ሚዛን የትርፍና ኪሳራ መግለጫ እንዲሁም ባለፈው የሂሳብ ማጠቃለያ ስራ ጊዜ ስለ ማኅበሩ ሁኔታና አሰራር ሪፖርት ያደራጃል።

3.ለጠቅላላ ጉባዔ ጥሪ ከመደረጉ በፊት የንብረት ዝርዝር መዝገብ፣ የሂሳብ ሚዛን፣ ትርፍ ኪሳራ ሂሳብ፣ የዲሬክተሮች ሪፖርት ለኦዲተር ተዘጋጅተው መስጠት አለባቸው፣ በዚህ ጊዜ እነዚህ ሰነዶች ለሚመለከተው ንግድ ሚኒስቴር መተላለፍ አለባቸው።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ NATIONAL BANK OF ETHIOPIA 52

## አንቀፅ አሥራ ሰባት

## የማኅበሩ ኦዲተር

1.የማኅበሩ ጠቅላላ ስብሰባ ኦዲተር ይሾማል። የሚሾመው ኦዲተር በሂሳብ ምርመራ ስራ የተፈቀደለት ሰው ወይም ድርጅት ይሆናል። የዚህ ኦዲተር ተግባር ስልጣንና ኃላፊነት በሕግ በተለይም በንግድ ሕግ አንቀጽ 348 መሰረት ይሆናል።

2.ታፈስ፣ ሺሰማ እና አያሌው የኦዲት አገልግሎት የህብረት ሽርክና ማኅበር የማኅበሩ ኦዲተር ሆኖ ተሹሟል።

3.የኦዲተሩ የስራ ዘመን ሦስት ዓመት ይሆናል።

## አንቀፅ አሥራ ስምንት

## የማኅበሩ ቆይታ

ማኅበሩ የተቋቋመው ላልተወሰነ ጊዜ ሲሆን በንግድ ሕጉ ቁጥር 473 ስር በተገለፁት ምክንያቶች ሊፈርስ ይችላል።

## አንቀፅ አስራ ዘጠኝ

## ጠቅላላ

**በዚህ የመመስረቻ ጽሑፍ ውስጥ ባልተገለፁት የማኅበሩ ጉዳዮች ላይ ሁሉ እንደ አስፈላጊነቱ የንግድ ሕጉ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ።**

**ይህ የመመስረቻ ፅሁፍ ዛሬ ------------------------------ በባለአክሲዮኖች በአዲስ አበባ ከተማ ተፈረመ።**

| <u>የባለአክሲዮኑ ሥም</u> | <u>ሙሉ ስምና ፊርማ</u> |
|---|---|
| 1.ኮ/ል ትዕግስቱ ሣህሌ ጊቤ | ______________________ |
| 2.ወ/ት አድያም ትዕግስቱ ሣህሌ | ______________________ |
| 3.ወ/ሮ ሊድያ ትዕግስቱ ሣህሌ | ______________________ |
| 4.አቶ መሰይ ትዕግስቱ ሣህሌ | ______________________ |
| 5.ዶ/ር ፊቨን ትዕግስቱ ሣህሌ | ______________________ |
| 6.አቶ ኃይለሚካኤል ከምባታ አላካ | ______________________ |
| 7.ወ/ሮ አሰለፈች ኀ/ስላሴ ተሰማ | ______________________ |
| 8.ወ/ሮ ሲሳይ ኃይለሚካኤል ከምባታ | ______________________ |
| 9.አቶ አቤል ኃይለሚካኤል ከምባታ | ______________________ |

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
52
NATIONAL BANK OF ETHIOPIA